የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

| አሥራ ሰባተኛ ዓመት ቁጥር ፷፯<br>አዲስ አበባ ግንቦት ፲፮ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም. | በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ<br>የሕዝቦች ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | 17th Year No. 67<br>ADDIS ABABA 24th May 2011 |
|---|---|---|

ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፪፻፴፭/፪ሺ፫

የአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ እንደገና ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ............................ ገጽ ፭ሺ፰፻፹፫

CONTENTS

Regulation No. 235/2011

**Arba Minch University Re-establishment Council of Ministers Regulation ..........................................Page 5883**

## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፴፭/፪ሺ፫

## አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲን እንደገና ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፩/፪ሺ፪ አንቀጽ ፭ እና በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር ፮፻፶/፪ሺ፩ አንቀጽ ፭(፩) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል ፡፡

፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ እንደገና ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፴፭/፪ሺ፫" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ፡፡

፪. መቋቋም

፩/ አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ (ከዚህ በኋላ "ዩኒቨርሲቲ" እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ሆኖ በዚህ ደንብ እንደገና ተቋቁሟል፡፡

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION No. 235/2011

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE RE-ESTABLISHMENT OF THE ARBA MINCH UNIVERSITY

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 691/2010 and Article 5(1) of the Higher Education Proclamation No. 650/2009.

1. **Short Title**

This Regulation may be cited as the "Arba Minch University Re-establishment Council of Ministers Regulation No. 235/2011."

2. **Establishment**

1/ The Arba Minch University (hereinafter the "University") is hereby re-established as an autonomous higher education public institution having its own legal personality.

ያንዱ ዋጋ Unit Price 2.30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፹ሺ፩
Negarit Gazeta P.O.box 80,001

፪/ የዩኒቨርሲቲው ተጠሪነት ለትምህርት ሚኒስቴር ይሆናል ::

፫/ ዩኒቨርሲቲው በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር ፮፻፶/፪ሺ፩ እና በፌዴራል ዩኒቨርሲቲዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፲/፪ሺ፫ መሠረት ይተዳደራል ::

፫. <u>ዋና ግቢ</u>

የዩኒቨርሲቲው ዋናው ግቢ አርባ ምንጭ ከተማ ሆኖ በሌሎች ቦታዎች የትምህርት ክፍሎች እና የምርምርና የሕብረተሰብ አገልግሎት ማዕከሎችን ሊያቋቁም ይችላል ::

፬. <u>የተሻረ ደንብ</u>

የአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፲፩/፲፱፻፺፮ በዚህ ደንብ ተሽሯል።

፭. <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ ግንቦት ፲፮ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም.

መለስ ዜናዊ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ጠቅላይ ሚኒስትር

2/ The University shall be accountable to the Ministry of Education.

3/ The University shall be governed by the Higher Education Proclamation No. 650/2009 and the Federal Universities Council of Ministers Regulation No.210/2011.

**3. <u>Main Campus</u>**

The University shall have its main campus at Arba Minch and may establish elsewhere other academic units and centers of research and community services.

**4. <u>Repealed Regulation</u>**

The Arba Minch University Establishement Council of Ministers Regulation No.111/2004 is hereby repealed.

**5. <u>Effective Date</u>**

This Regulation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa, this 24th day of May, 2011.

MELES ZENAWI

PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA